ቁጥር OFAGF-03.5/
ቀን 14/07/20—

ለተከበሩ አቶ ታገሰ ጫፎ
የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈጉባኤ

ለክብርት ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ
የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ
<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- <u>የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድን የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርትን ይመለከታል</u>

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 9 ገጽ ኦዲት ሪፖርት እና 12 ገጽ የሂሳብ ሪፖርቶች በድምሩ 21 ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን እንገለጻለን፡፡

ከማክበር ሠላምታ ጋር

ጌታሁን ዳምጤ
የፋይናንስና ኮምፕሊያንስ መ/ቤቶች
ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ

የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ
ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት /2015 ዓ.ም
አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ

የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ

ኦዲት ሪፖርት

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የተመደበለትን የመደበኛ እና የካፒታል በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፤ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ስራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው ::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን ሲሆን ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች በመከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና ሪፖርቶችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶች ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል::

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑንና በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የፌዴራል ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በመ/ቤቱ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ ሪፖርቶች፤

- የገቢ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ማመዛዘኛ፣

ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የ2014 የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል የተዘጋጁና፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን ጠብቆ የተከናወነ በመሆኑ በእኛ አስተያየት በቦርዱ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች እና የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓቱ አጥጋቢ ሆኖ ተገኝቷል፡

ምንም እንኳ ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የማይቀይረው ቢሆንም ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች (Emphasise Matters)

1. የፌደራል መንግስት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል ሶስት አንቀፅ 12 ተራ ቁጥር 1 ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት ለበጀት አመቱ የተፈቀደለትን የመደበኛና የካፒታል በጀት አጠቃቀም በሚገባ መቆጣጠር እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ቦርዱ የበጀት አጠቃቀሙን በመመሪያው መሰረት እያከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ እንዲቻል በ2014 በጀት ዓመት ለቦርዱ ከተፈቀደው የመደበኛ በጀት ውስጥ በየፕሮግራሙ ከ10% (በመቶ) በላይ ያልተሰራበት በጀት መኖሩን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

   ከመደበኛ በጀት በድምር ብር 40,057,458.71 ስራ ላይ ያልዋለ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)

1. የንብረት አመዘጋገብ ፣አያያዝ እና አጠባበቅን በተመለከተ፤

ፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ንዑስ 5 የመንግሥት መስሪያ ቤቶች በእጃቸው ያለውን የመንግሥት ንብረት በጥንቃቄ የመያዝ፤ የመጠቀም፤ የመቆጣጠር እና አገልግሎቱ ሲያበቃ ወይም አገልግሎት ላይ በማይውሉበት ጊዜ በወቅቱ በተገቢው መንገድ እንዲወገዱ የሚል ሲሆን በዚሁ መሰረት ተቋሙ ኦዲት ሲደረግ፡-

በዋናው ግቢ የቋሚ እቃዎች እስቶር በተመለከተ

- በቋሚ እቃዎች ላይ መለያ ቁጥር/ታግ/ ያልተለጠፈ መሆኑና በእስቶር ውስጥ ለሚገኙ እቃዎች ቢን ካርድ ያልተዘጋጀላቸው መሆኑ፤
- በቋሚ እቃ እስቶር ውስጥ እቃዎችን ገቢና ወጪ የማድረግ በአንድ ሰራተኛ መሆኑ፤

በሳሪስ የስልጠና ማዕከል የሚገኙ ንብረቶች በተመለከተ

ኦሮሚያ አዳራሽ

- በሳሪስ የስልጠና ማዕከል በኦሮሚያ አዳራሽ የመወገድ በርካታ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች (ቅፆች) የሚገኙ መሆኑ፤
- በኦሮሚያ አዳራሽ ከምርጫ በኋላ ተመላሽ የተደረጉ መቀስ ፣ ፕላስተር እና የፕላስተር መቁረጫ በጠባብ ክፍል ውስጥ ተደራርበው እና ተጫጭነው የተቀመጡ መሆኑ፤
- የአዳራሹ ክፍል አቧራ ስለሆነ ንብረቶን በቀወላሉ ለብልሽ የሚዳርግ መሆኑ፤
- በአዳራሽ በር ላይ በርካታ መወገድ የሚችሉ የፕላስቲክ ቁሶች የሚገኙ መሆኑ፣
- በርካታ የድምፅ መስጫ ሳጥን ለብልሽት በተጋለጠ መልኩ ከውጪ ፀሀይ ላይ የተቀመጡ መሆኑ፣

አላቂ እቃዎች ስቶር

- የሚወገድ GPR/18 ብዛት 13 በስቶር ውስጥ የሚገኝ መሆኑ፤

ቋሚ እቃዎች ስቶር

በስቶሩ ጥበት ምክንያት ብሉ ቦክስ (Blue box) ተደራርቦ ስለሚገኝ በብሉ ቦክሱ ውስጥ የሚገኙ ታብሌቶች፣ የአይ.ሲ.ቲ ዕቃዎች እና የመሳሰሉት በቀላሉ ለብልሽት በሚያጋልጥ መልኩ የተቀመጡ መሆኑ፤

የመኪና ስፔር ፓርት ስቶር

ቢሮ ቁጥር 11 ተመላሽ የሆኑ የተለያዩ የተሽከርካሪ ስፔር ፓርት የሚገኙ መሆኑ፤

ደቡብ አዳራሽ

- ሳሪስ የስልጠና ማዕከል ቢጫ ፎቅ ዙሪያ በርካታ ብረታ ብረት የሚገኝ መሆኑ፣
- በማዕከል መወገድ ያለበት የተሽከርካሪ ጎማዎች ብዛት 278 እና የእንጨት ፈርኒቸር ውጪ ላይ ተቀምተው የሚገኝ መሆኑ፣
- በሳሪስ የስልጠና ማዕከል ከምርጫ በኋላ ተመላሽ የተደረጉ ታብሌቶች ፣ ፕሪንተሮች፣ ላፕቶፕ ኮምፒውተሮች፣ ጀኔሬተሮች የሚሰሩ እና የማይሰሩ ተብለው ሳይረጋገጥ የሚቀበሉ እና ተለይተው ያልተቀመጡ መሆኑ፤

በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡

2. የተሽከርካሪዎች አስተዳደር በተመለከተ፤

የፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 አንቀጽ 5 የመመሪያው አላማ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በእጃቸው ያለውን የመንግስት ንብረት በጥንቃቄ የመያዝ፤የመጠቀም የመቆጣጠር እና አገልግሎት ላይ በማይውልበት ጊዜ በወቅቱና በተገቢው መንገድ ማስወገድ እንዳለበት ያዛል። በዚህ መሰረት የአስተዳደሩ የተሽከርካሪዎች አመዘጋገብ፣ አያያዝ እና አጠባበቅ ኦዲት ሲደረግ ቦርዱ ካሉት ተሽከርካሪዎች ዉስጥ፡-

- የሰሌዳ ቁጥር U.N -0078 ቶዮታ ኮሮላ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ወደ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት ያልዞረ መሆኑ፤
- የሰሌዳ ቁጥር ኢ.ት. 4-10696 ስቴሽዋጋን የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌለ መሆኑ፤
- አንድ ሞተር ሳይክ ሠሌዳ ቁጥር ኢ.ት. 4-0013 እና ሶስት ተሽከርካሪ ሠሌዳ ቁጥር ኢ.ት4-18720፣ ኢ.ት4-13005 እና ኢ.ት4-13007 በብልሽ ምክንያት አገልግሎት የማይሰጡና ሳሪስ አከባቢ በሚገኘው ንብረት ክፍል ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፣

በኦዲት ወቅታ ታውቋል፡፡

3. የክትትል ኦዲት በተመለከተ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል በወጣ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ክፍል አምስት አንቀጽ 17/3 መሰረት ተመርማሪ መሥሪያ ቤቶች በፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተላኩ ሪፖርቶች በተገለፁ ግኝቶች ላይ ተገቢውን የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ በተሰጡ የማሻሻያ ሃሣቦችና አስተያየቶች መሠረት ከ15 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ አለባቸው፡፡ የወሰዱትን እርምጃ እና ለመውሰድ ካልቻሉ ምክንያቱን በመግለጽ ለፌዴራል ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት ከላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማሳወቅ አለባቸው፡፡ በዚህ መሰረት ቦርዱ የባለፉት በጀት ዓመታት ኦዲት ሪፖርት በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሠረት እርምጃ ስለመወሰዱ ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

በ2013 በጀት ዓመት ኦዲት ግኝቶች በተመለከተ:

1. ከቦርዱ ዋና ሰብሳቢ፣ ም/ዋና ሰብሳቢ እና የቦርዱ አባላት ደመወዝ ተቀናሽ መደረግ የሚገባው የህክምና መዋጮ በድምሩ ብር 19,655.36 ተቀንሶ ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤
2. በተለያዩ ቀናትና የወጪ ማስመሰከሪያዎች በድምሩ ብር 2,740,275.76 ለፖለቲካ ፓርቲዎች ድጋፍ የተከፈለ ቢሆንም ገንዘቡን መቀበላቸውን የሚያሳይ የገንዘብ ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበለት መሆኑ፤
3. በድምሩ ብር 218,565.50 ለአጀቢዎች እና ለሹፌሮች አለአግባብ የምሳና የእራት አበል ክፍያ ያልተመለሰ መሆኑ፤
4. የቦርዱ ሰብሳቢ መኖሪያ ቤት እድሳት፣ አጥር በአደገኛ ሽቦ ለማሳጠር በድምሩ ብር 233,037.84 ያለአግባብ ለቦርዱ ከተፈቀደው በጀት እንዲጠገን በመደረጉ ወጪ የሆነው ገንዘብ ከፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን እንዲተካ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ያልተተካ መሆኑ፤

የ2012 በጀት ዓመት ኦዲት ግኝቶች በተመለከተ:

ከሀምሌ1/2011 እስከ ሰኔ 30 2012 ድረስ ከቦርዱ ዋና ሰብሳቢና ም/ዋና ሰብሳቢዎች በመመሪያው መሰረት ከደመወዛቸው ያልተቀነሰ የህክምና መዋጮ (2%) በድምሩ ብር 19,983.12 ተቀናሽ ተደርጎ ለሚመለከተው አካል ገቢ ሊደረግ እንደሚገባ አስተያየት ቢሰጥም እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ::

የ2011 በጀት ዓመት ክትትል ኦዲት;

የተሟላ ማስረጃ ሳይኖር ለስልጠና ተብሎ ከተከፈለው ብር 240,643.36 ውስጥ ብር 200,719.96 ማስረጃ የቀረበለት ቢሆንም ቀሪው ብር 39,923.40 ማስረጃ እንዲቀርብ አስተያየት ቢሰጥም እርምጃ ሳይወሰድበት ተገኝቷል::

የ2010 በጀት ዓመት ክትትል ኦዲት;

1. ተቀናሽ የተደረገ ግብር በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ገቢ ባለመደረጉ የተከፈለ የቅጣት ክፍያ ብር 1,125,076.41. በተመከተ አለአግባብ ክፍያ በመፈፀሙ የሥራ ኃላፊዎች ተጠያቂ ሊደረጉ እንደሚገባ አስተያየት ቢሰጥም እርምጃ ለመወሰዱ ማስረጃ አልቀረበም::

2. ማስረጃ ያልቀረበለት ለህክምና ወጪ ከተደረገው ብር 2,156,148.55 ውስጥ ብር 1,582,153.26 ማስረጃ የቀረበለት ሲሆን ቀሪው ብር 573,995.29. ማስረጃ እንዲቀርብ አስተያየት ቢሰጥም ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ ታውቋል፡፡

የ2009 በጀት ዓመት

በድምር ብር 342,850.95 ያለ አግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡

የህግ ጉዳዮች በተመለከተ (Compliance Issue)፣

1. **ተቀናሽ ያልተደረገ የህክምና መዋጮ፤**

የፌዴራል መንግስት ከፍተኛ ኃላፊዎች በውጭ አገር ነጻ ሕክምና እንዲያገኙ ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 5.1 እና 5.2 ላይ እንደተመለከተው የውጭ አገር ሕክምና የተፈቀደላቸው የከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎች በየወሩ ከደመወዛቸው እንደ የሃላፊነታቸው 1% ወይም 2% (አንድ ወይም ሁለት በመቶ) የህክምና መዋጮ መቁረጥ እንደሚገባቸው ይደነግጋል፡፡ ስለሆነም ከቦርዱ ኃላፊዎች የህክምና መዋጮ በመመሪያው መሰረት ተቀናሽ የሚደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

በድምሩ ብር 17,485.23 ከሀምሌ1/2013 እስከ መጋቢት/2014 ድረስ ከቦርዱ ኃላፊዎች የህክምና መዋጮ በመመሪያው መሰረት ከደመወዛቸው ተቀናሽ ሳይደረግ ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን በ2013 በጀት ዓመት ኦዲት ወቅት ተመሳሳይ ግኝት ተገኝቶ የኦዲት አስተያየት ቢሰጥም አሁንም ያልተስተካከለ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

2. **የክፍያ ተመን ሳይወጣ ለምርጫ ተሳታፊዎች የተከፈለ አበል በተመለከተ**

የፌደራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 4፣7 ክፍያ ለሚፈፀምባቸው ወጪዎች ተገቢውን የሰነድ ማስረጃ መቅረቡን፤ ወጪ ከመደረጉ በፊት ሰለወጪው የተሟላ ማስረጃ ማቅረብና ሥልጣን ባለው አካል መፈቀድ እንዳለበት ይገልጻል፡፡

ይሁን እንጂ በሀገር አቀፍ ምርጫ ለተሳተፉ ሰራተኞች ክፍያ ሲፈጸም በሚመለከተው አካል የጸደቀ የክፍያ ተመን መመሪያ ሳይኖር በድምሩ ብር 386,573,686.00 ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

3. <u>ከስልጣን ገደብ በላይ የጸደቀ የወጪ ሂሳብ፣</u>

የፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 ክፍል አራት የፋይናንስ ኃላፊነት በሚለው በአንቀጽ 6 የመንግሥት መስሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች የፋይናንስ ኃላፊነት፤ በተራ ቁጥር 3 የፋይናንስ ጉዳዮችን በተመለከተ ስለሚሰጥ የሥልጣን ውክልና በሚለው አንቀጽ ስር ፊደል ለ የመስሪያ ቤቶች ኃላፊዎች ዝርዝር የፋይናንስ ጉዳዮችን በተመለከተ የፋይናንስ ሥራ ለሚያከናውን የሥራ ክፍል ኃላፊ ውክልና መስጠት ይኖርባቸዋል ይላል:: ተወካዩም ለሌሎች በፋይናንስ የሥራ ሂዳት ለተመደቡ ሠራተኞች መወከል የሚችልበት ኃላፊነት ሊሰጠው ይችላል:: እንዲህ አይነቱ ውክልና ሲሰጥ የውክልናው ዓይነት እና የሥልጣን ገደቡ በጽሁፍ መደረግ እንዳለበት ይገልጻል::

ይሁን እንጂ የፋይናንስ ስራ አስኪያጅ ለቦርዱ መደበኛ የስራ በጀት ከተመደበው በአንድ ጊዜ እስከ 10,000.00 ብቻ በቼክ ወጪ ተደርጎ እንዲከፈል፣ የመወሰንና የመፈረም ስልጣን ከቦርዱ የበላይ ኃላፊ ውክልና የተሰጣቸው ቢሆንም በተለያዩ የወጪ ማስመስከሪያዎች በድምሩ ብር 11,160,800 እንዲያጸድቁ ከተሰጣቸው የስልጣን ገደብ በላይ ወጪውን በማጽደቅ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲት ታውቋል::

4. <u>ለሶስተኛ ወገን የተሰጠ የጥበቃ እና የጽዳት አገልግሎትን በተመለከተ፤</u>

የፌዴራል የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁ.1064/2010 አንቀጽ 22/1 አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ማንኛውም መ/ቤት ሚኒስቴሩን በማስፈቀድ የህዝብን ጥቅም በማይጎዱ የተወሰኑ የስራ መደቦችን ወይም ሥራዎችን ለግል ድርጅቶች ወይም ለሌሎች ተቋማት በውል በማሸጋገር እንዲሰሩ ማድረግ እንደሚቻል ይደነግጋል። እንዲሁም የፌዴራል መንግስት ግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ 2002 በወጣው ክፍል አንድ አንቀጽ 4 ፊደል ሀ በግዥ አፈጻጸም ረገድ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ማስገኘት እንደሚገባ ይህም ማለት ቁጠባን፣ የአፈጻጸም ብቃትን እና ውጤታማነትን ማረጋገጥ እንዳለበት ይገልጻል።

ይሁን እንጂ ቦርዱ ከሎያል ሴኪዩሪቲ ኤጀንሲ የጥበቃ አገልግሎት ግዥ በመፈጸም ውል የያዘ ቢሆንም:-

➡ ወደ ግዥ ሂደቱ ከመግባቱ በፊት ስራዎቹን ለሶስተኛ ወገን ለማሸጋገር ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ፈቃድ ሳይጠየቅ ስራዎቹ ለሶስተኛ ወገን የተሰጡ መሆኑ፣

➡ ስራዎቹ ለሶስተኛ ወገን ከመሰጠቱ በፊት ከሰው ሃይል እንዲሁም ከመንግስት ውስን ሃብት አኳያ የአዋጭነት ጥናት የተሰራበት ማስረጃ የሌለ በመሆኑ፣

በድምሩ ብር 1,079,999.96 የግዥ ሂደቱን ሳይከተል የጥበቃ አገልግሎት ግዥ ከሶስተኛ ወገን በማከናወን ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ ታውቋል፡፡

5. <u>በወቅቱ ያልተወራረዱ ተሰብሳቢ ሂሳቦች፣</u>

በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ፣ በመመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ደግሞ ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል። ቦርዱ ተሰብሳቢ ሂሳቦችን በደንቡና በመመሪያው መሰረት በወቅቱ እያወራረደ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

በድምሩ ብር 64,015,582.88 ተሰብሳቢ ሂሳብ የሚታይ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 56,298,092.70 ከ1 ዓመት እስከ አምስት ዓመት፣ ብር 4,358,325.82 ከአምስት እስከ 10 ዓመት እና ብር 3,359,164.36 ከ10 ዓመት በላይ ሳይሰበሰብ የቆየ ውዝፍ የተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

6. <u>በወቅቱ ያልተከፈለ የተከፋይ ሂሳብ፣</u>

በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 5/ሐ የተለያዩ አካላት ቀንሰው ያስቀሩትን የግብር እና ሌሎች ሂሳቦች ለሚመለከተው ግብር አስገቢ አካል ወቅቱን ጠብቀው ማስተላለፍ እንዳለበት ያስቀምጣል፡፡

ይሁን እንጂ በቦርድ የ2014 በጀት ዓመት የሂሳብ ሪፖርት በድምሩ ብር 590,268.47 በወቅቱ ያልተከፈለ ውዝፍ የተከፋይ ሂሳብ መኖሩ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት